# የመለስ አሳፋሪ ቀልድና ትርጉሙ

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 61 ርዕሰ አንቀጽ

መለስ አፋኝ ህጎችን ለማጽደቅ እጅ በማውጣት የደከሙትን፣ ‹‹የተከበሩ የፓርላማ አባላት›› የተሰኙት አሻንጉሊቶቹን ሰኔ 29 ቀንም እንደልማዱ ቁንጠኛ ግን አሳፋሪ በሆነ ቀልድ አስቆ ተዝናንቶባቸዋል፡፡ መለስ የዚህን ቀልድ መነሻ ሃሳብ ያገኘው ለኤክትሪክ ኃይል መቋረጥ ማን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት ከተነሳው ‹‹ፈታኝ›› ጥያቄ ነው፡፡ የምክር ቤቱ ግንባር ቀደም ፈላስፎች ይቅርታ ጠያቂን በመፈለግ አድካሚ የአዕምሮ ሥራ ላይ ተጠምደው እያለ የመለስ ‹‹ፈጣን›› ጭንቅላት ‹‹ለኤሌክትሪክ መቋረጥ ተጠያቂውና ዋነኛው ይቅርታ ጠያቂ ድህነት ነው›› በማለት የወሩን ታላቅ ቀልድ ፈለሰፈ፡፡ አድራሹ በሳቅ ተናወጠ፡፡ በተለይ ራሱ መለስ በተቀመጠበት ክንፍ የነበሩት አሻንጉሊቶች በጌታቸው ‹‹ብልህነት›› በአድናቆት ተፍነከነኩ፡፡ እሱ ግን ግንባሩን ቅጭም አድርጎ ቀጠለ ‹‹... ከዚያ ቀጥሎ አስተሳሰባችን፣ የመንግሥት የዕቅድ አወጣጥና አፈጻጸም ውስንነት ነው፡፡ ሁሉም በየደረጃቸው ይቅርታ መጠየቅ ይችላሉ ...›› ... ቀጠለ ... አጋጣሚውን ተጠቅሞም አበዳሪዎች ሊገባቸው ስላልቻለው ፈጣን እድገት ተናገረ .... የእድገቱን ፍጥነት ተገንዝበው እርዳታና ብድር እሱ በፈለገው ጊዜና መጠን ስላልሰጡት ለጋሾቹን ወረፋቸው ... ቀጠለ ...ቀጠለ .. ብዙ ተናገረ፡፡

‹‹የተከበሩ›› በተባለ አሮጌ ቡልኮ የተሸፋፈኑት አሻንጉሊቶች በመጀመሪያ ቀልዱ፣ ቀጥሎ ደግሞ ውረፋው አዘናግቷቸውም ነው መሰል አቶ ወይም ወ/ሮ ድህነት መቸ መጥተው ይቅርታ እንደሚጠይቁ ቀጠሮ ሳይዙ ተበተኑ፡፡ ይህንን መራር ቀልድና ሽሙጥ አሻንጉሊቶቹ ስቀዉ ቢያልፉትም የወያኔን የወረደ አስተሳሰብ አጉልቶ የሚያሳይ አባባል በመሆኑ እኛ በቀላሉ ልናልፈው አልፈቀድንም፡፡

ለመለስ የመሃይም ቀልድ የምናቀርበው የመጀሪያው ጥያቄ ‹‹ለመሆኑ ድህነት ራሱ ውጤት አይደለምን?›› የሚል ይሆናል፡፡ ድህነትን ራሱ ማን ፈጠረው፣ ከየት መጣ፣ እንዴት መጣ፣ ከየት የት ደረሰ ...? አምና ከተሞችን ያሸበቀረው መፈክር ‹‹ድህነትን ተረት እናደርጋለን!!!›› የሚል አልነበረምን? ታድያ ተረት ሊሆን የተቃረበው ድህነት እንደምን ለዘንድሮው ኤሌክትሪክ መቋረጥ ምክንያት ሊሆን ቻለ? ከአስራ ስምንት ዓመታት ያልተቋረጠ ፈጣን እድገት በኋላ ድህነት በምን አቅሙ ነው ኤሌክትሪክን ያህል ነገር ሊያቆም የቻለው?

በመፈክር የተገነባ ኢኮኖሚ መፈክሩ ሲወይብ አብሮ እንደሚወይብ ይህ አንድ አቢይ ማረጋገጫ ነው፡፡ የወያኔ የውሸት ቁጥሮች እና መረን የለቀቁ መፈክሮች እንዲህ ዳገት ላይ ይለግማሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ እንደሚያውቀው ድህነት የወያኔ ወዳጅ ነው፡፡ ድህነት ለወያኔ ምን ያልሆነው ነገር አለ? ቀዳሚ አጀንዳዬ ‹‹ድህነት ቅነሳ›› ነው በማለት ጥቂት የዋህ ኢትዮጵያዊያንን፣ በርካታ የውጭ አገር ዜጎችን እና መንግሥታትን ያጭበረብርበታል፡፡ ድህነት ለነመለስ የግል ኪስ እና ለኤፈርት የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ ነው፡፡ እነሆ አሁን

ደግሞ ኤሌክትሪክም ሲጠፋ በኃላፊነት የሚጠየቅና በይቅርታ የሚታለፍ ሆኗል፡፡ ድህነት የወያኔ ባለውለታ ነው፡፡

እንዲያው ለነገሩ የግልገል ግቢ ፕሮጀክቶች ጨረታ ጉዳይ በኢጣልያ ፓርላማ እንዲነሳ ያደረገው፤ በዓለም ባንክም ውዝግብ እንዲነሳ ያደረገው ድህነት ነው ወይስ ..ሌላ..? ድህነት ጨረታ ውስጥ ምን ይሰራል? የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ወደ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ያከስሩታል ስለተባሉት የነፋስ ጄኔረተሮችስ ጉዳይ ተጠያቂው አሁምን ድህነት ነው? የናፍጣ ጄኔሬተር ገበያ የደራላቸው የድህነት ወዳጆችስ እነማን ናቸው?

የመለስን አፀያፊ ቀልድ ሰምተው በአድናቆት የተንተከተኩት ‹‹የሕዝብ ተወካይ›› ተብየ የወያኔ ጉልቶች ከተናጋሪዉ ባላነሰ ግምት ውስጥ ጥሏቸዋል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲ የሕዝብ ተወካዮችም መለስን በጥያቄ ለማጣደፍ ባይታደሉም እንኳን ለእነሱ በተደጋጋሚ እንደሚባለው ሁሉ ‹‹ቀልዱ የም/ቤቱን ክብር አይመጥንም›› ማለት እንኳን አለመቻላቸው ለትዝብት ዳርጓቸዋል፡፡ ለመሆኑ መለስ ከዚህ በላይ ምን ሲያደርግ ነው መሮዓቸው አዳራሹን ለቀው የሚወጡት?

ቀድሞም የምናውቀው ቢሆንም እንኳን በዚህ ቀልድ መለስ እና ተጠያቂነት የማይተዋወቁ መሆኑን ነግሮናል፡፡ መለስ ፈጽሞ የሌሉ መልካም ውጤቶችን ፈጥሮ ራሱን ሲያሞካሽ ላፈጠጡ ጉድለቶች ግን ሁሌም ተጠያቂው ሌላ አካል ነው፡፡ እስካሁን በተደጋጋሚ የምንሰማቸው ተጠያቂዎች የነፍጠኛው ሥርዓትና ነፍጠኞች፣ ተቃዋሚዎች፣ የኤርትራ መንግሥት፣ የሶማሊያ ታጣቂዎች፣ የእርዳታ ድርጅቶች፣ ስግብግብ ነጋዴዎች፣ ጥገኛ ባለሃብቶች …. ወዘተ ነበሩ፡፡ እራሱ ላደረሳቸው ጥፋቶች አቅሙ የቻለውን ያህል ‹‹ተጠያቂዎች ናቸው›› ያላቸውን ገድሏል፣ አስሯል፣ አንገላቷል፡፡ አንዳዶቹ ፈጽሞ ለማያውቁት ጥፋት ይቅርታ እንዲጠይቁ ተገደዋል፡፡ አሁን ከችግሩ መስፋት ጋር ለጋሽ አገሮች፣ ድህነት፣ እና አስተሳሰብ በተጠያቂዎች ዝርዝር ውስጥ ገብተዋል፡፡ እንደተነገረን ከሆነ እነዚህኞቹ እንደፊተኞቹ አይገደሉም፣ አይታሰሩም፣ አይገላቱም፤ ይቅርታ ብቻ ነው የሚጠይቁት፡፡

ሌላው በጣም ግልጽ የሆነ ጉዳይ የመለስ መንግሥት ምን ያህል የእርዳታና የብድር ጥገኛ መሆኑን ነው፡፡ ‹‹ጥገኛ›› የሚለውን ቃል በጣም ያስተዋወቀው ራሱ መለስ ሲሆን ሲጠቀምበት የኖረውም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሊያስወግዳቸው የሚፈልጋቸውን አካላት አጥላልቶና አዋርዶ ለማቅረብ ነበር፡፡ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በደረሰው ቀውስና ለዚህም በሰጠው ምሳሽ ግን ከምንም በላይ የራሱን ሥር የሰደደ ጥገኝነትን ነው የነገረን፡፡ እርሱና የመሠረተው መንግሥት ከእርዳታ ውጭ አስትንፋስ የሌላቸው መሆኑን ነው ሳያውቀው ይፋ ያደረገው፡፡

ቀጥሎም የፈጣን እድገት ድርሰቱ ወዳጆቹም ጭምር መጠራጠር መጀመራቸው ምን ያህል እንዳበሳጨው እንድንገነዘብ ረድቶናል፡፡ ለጋሽ አገሮች የአስራ ምናምን በመቶ እድገት ሪፖርቱን አምነው ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ገንዘብ ባበደሩኝ ነበር ብሎ መቆጨቱ የውሸቶቹ የማሳመን ችሎታ መለስን ባሸበረ መጠን መሸርሸሩን ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም ወያኔ ይዘው ይጨብጠው ማጣቱና አጠቃላይ የሆነ የተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ መድረሱን ያመለክታል፡፡ በአንድ በኩል ሰሞኑን ያገረሸበት ‹‹ፓርቲዬ ከፈቀደልኝ ሥልጣኔን መልቀቅ እፈልጋለሁ›› የሚል ወሬ መንዛትና ማዝነዛት እና ዘወር ብሎ ውስጥ ለውጥ ለወዳጆቹ ‹‹ለምኑኝ›› እያለ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አስካሁን ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂው ድህነት እንጂ እኔ አይደለሁም ማለቱ የወያኔ ‹‹የፍራሽ ማደስ›› ፕሮጀት አካላት ናቸው፡፡

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤ መለስና ጓደኞቹ ድህነትን እየቀለቡ እንዲያላግጡብን ፈጽሞ አንፈቅድላቸውም፡፡ ከዚህም በፊት ደጋግመን እንዳልነው አገራችንን ከድህነት ለማውጣት የመጀመሪው ወሳኝ እርምጃ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በተባበረ ክንዳችን በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን እናደርገዋለን፡፡

http://www.ginbot7.org/News_Paper/Ginbot_7_Dimts_Issue_No61.pdf